1. አመልካች በዋስትና ውል በተመለከተው መሠረት ለመክፈል የሚገደደው ብር ስልሳ ሺህ (60,000) ብቻ ነው ብለን የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የመ/ቁ 62171 መጋቢት 22/2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስነናል፡፡
2. በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የተወሰነውን ቀሪ የካሣ ገንዘብ የሥር አንደኛ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ተሻሽሎ በተወሰነው መሠረት የኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 48698

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ ሣሙኤል ዓለሙ - ጠበቃ ፈቃዱ አስፋው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ኩባንያ የመድን ሽፋን የገባሁለት የሠ.ቁ 3-34603 የሆነ መኪና በደረሰበት አደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ በመድን ውሉ መሠረት ተከሳሽ ተገቢውን ካሣ እንዲከፍለኝ ብጠይቅም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ጉዳት የደረሰበትን መኪናዬን ሙሉ ዋጋ ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሣ አምስት ሺህ) እንደዚሁም መኪናው በጊዜው ባለመጠገኑ ወይንም ዋጋውን ባለመክፈሉ ምክንያት በከሳሽ ላይ የደረሰውን የጥቅም መቋረጥ ብር 58,000(ሃምሣ ስምንት ሺህ) ጨምሮ ክሱ ካስከተለው ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ከመድን ውሉ ውጭ ሁለት ሰዎችን ጭኖ ሲያጓጉዝ ሲሆን የመድን ሽፋን የተገባው ጭነት ጭኖ ሲጓጓዝ ለሚደርስ ጉዳት ነው፡፡ ስለሆነም የከሳሽ መኪና ሰው ጭኖ ሲጓጓዝ ለደረሰው ጉዳት ከመድን ውሉ አኳያ ተከሳሽ ካሣ ለመክፈል ግዴታ የለበትም፡፡ የክፍያ መጠኑን በተመለከተም ከሳሽ የደረሰበት መኪና ሊጠገን የማይችል ስለመሆኑ ባላስረዱበት ሁኔታ ሙሉ ዋጋ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም፡፡ በመድን ውሉ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠንም መኪናው የመድን ሽፋን በተሰጠው ጊዜ የተገመተ እንጂ አሁን ያለውን የመኪና ዋጋ ስለማያስረዳ በዚህ ልክ ካሣ ሊከፈል አይገባም፡፡ በመድን ውሉ መሠረትም ተከሳሽ ለተቋረጠ ጥቅም ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ኃላፊነትን በተመለከተ ተከሳሽ በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ሰው ጭኖ ሲጓዝ እንጂ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ስላልሆነ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ቢከራከርም ሰው ጭኖ ጉዳት ስለመድረሱና የሰዎችን መጫን ከአደጋው ጋር ያለውን ግንኙነት አላስረዳም፡፡ ይልቁንም በማስረጃነት የቀረበው የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው መሐል መንገድ ላይ የገባን ሰው ለማዳን ሲሞክር መኪናው መንገዱን ስቶ ከዛፍ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት እንደሆነ የሚያረጋግጥ ስለሆነ ሰው ጭኖ መጓዙ የአደጋው መንስኤ ባለመሆኑ ተከሳሽ በመድን ውሉ መሠረት በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የካሣ መጠኑን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ጉዳት የደረሰበትን የከሳሽ መኪና በባለሙያ እንዲገመት አድርጎ ጉዳቱ በመቶኛ ሲሰላ 83.48% በገንዘብ ሲሰላ ደግሞ ብር 196,546.98(አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ከዘጠና ስምንት) አረጋግጦ ከ75% በላይ ጉዳት ከደረሰ እንደ ሙሉ ውድመት /Total loss/ ስለሚቆጠር የመኪናውም ግምት ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ) እንደሆነ ግራ ቀኙ ባደረጉት የመድን ውል ላይ ስለተመለከተ ተከሳሽ ይህንኑ ገንዘብ ለከሳሽ እንዲከፍል የተቋረጠ ጥቅምን በተመለከተ ግን በመኪናው ላይ የደረሰው ሙሉ ውድመት ስለሆነ ተከሳሽ ለመክፈል አይገድድም በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በተጠሪ መኪና ላይ በአደጋ ምክንያት ጉዳት በደረሰ ጊዜ 2 ሰው ጭኖ መገኘቱ ከመድን ውሉ አኳያ አመልካች ኃላፊ ነው መባሉ ተገቢነቱን ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጐ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተው መርምረናል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? በአግባቡ ነው ከተባለስ የካሣ ክፍያው መጠን ተገቢነት አለው ወይንስ የለውም? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ኃላፊ መባል የለብኝም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት ያደረሰው ሰው ጭኖ ሲጓዝ እንጂ ዕቃ ጭኖ ባለመሆኑ ከመድን ውሉ አኳያ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በመኪናው ላይ 2 ሰዎች ተጭነው እንደነበረ አምኖ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የተጫኑት የመኪናውን አገልግሎት ከዕቃ መጫን ሰው ወደመጫን አገልግሎት በመቀየር ሳይሆን በወቅቱ ተጭኖ የነበረው የመብራት ኃይል መ/ቤት ምሶሶዎችን ለመደገፍ፣ ለመጫንና ለማውረድ ተብሎ የጭነት ሥራ ለመሥራት ነው በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በመድን ውሉ መሠረት ካሣ ለመክፈል የምንገደደው መኪናው ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ለሚደርስበት ጉዳት እንጂ ሰው ጭኖ በሚጓዝበት ጊዜ አይደለም የሚል ክርክር ቢኖረውም የተጠሪ መኪና ሁለቱን ሰዎች የጫነው ከጭነት ሥራ ጋር በተያያዘ ያልተጫኑ ስለመሆኑና ሰዎችን ለማጓጓዝ ታስቦ የተጫኑ ስለመሆናቸው ማስረዳት የሚጠበቅበት ከመሆኑም በላይ ሰው የመጫኑም ሁኔታ ለአደጋው መንስኤ /Risk Possibility/ መሆኑንም ጭምር ማስረዳት ይጠበቅበታል ሆኖም ግን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ይልቁንም ጉዳት የደረሰው በጉዞ ላይ መሐል መንገድ ላይ የገባን ሰው ለማዳን ሹፌሩ ጥረት ሲያደርግ መንገዱን ስቶ በመውጣት ከዛፍ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት እንደሆነ በትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ላይ የተገለፀ ስለሆነ በተጠሪ መኪና ላይ የተጫኑት ሰዎች ኃላፊነቱን ከሚያስከትለው ሁኔታ ጋርም ሆነ ከካሣ ክፍያው ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ስለሌለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የካሣ ክፍያ መጠኑን በተመለከተ የተጠሪ መኪና ከአደጋው በኋላ ተገጭቶ ጉዳቱ በድምሩ ብር 196,546.98(መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር ከዘጠና ስምንት ሣንቲም) መሆኑ ተረጋግጧል የሥር ፍ/ቤቶች ለተጠሪ ካሣ እንዲከፈላቸው ውሣኔ የሰጡት የመኪናው ዋጋ ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ) እንደሆነ በመድን ውሉ ላይ ስለተመለከተ ይህንኑ አመልካች ለተጠሪ መክፈል አለበት በማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን ለአንድ ንብረት ወይም ዕቃ መድን የገባ ሰው ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 678 የተመለከተ ሲሆን የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳት የደረሰበት የተጠሪ መኪና በባለሙያ እንዲገመት ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ ግምቱ ሲቀርብ በዚሁ ግምት መሠረት ካሣ እንዲከፈል መወሰን ሲገባው ከግምት በኋላ ተመልሶ በመድን ውሉ ላይ የተቀመጠው የመኪናው ግምት እንዲከፈል መወሰኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 108121 በ12/2/2001 ዓ.ም. የሰጠው የኃላፊነት ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80957 ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. ይህንኑ የኃላፊነት ውሣኔ በማጽናት የሰጠውን ትዕዛዝ አጽንተናል፡፡ በሌላ በኩልም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በተጠቀሰው የመ/ቁጥር በ28/7/2001 ዓ.ም. አመልካች ብር 235.00 ካሣ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከንግድ ሕግ ቁጥር 678 ጋር ያልተገናዘበ ስለሆነ በፍብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት አሻሽለን የተጠሪ መኪና በጉዳቱ ጊዜ በተገመተው መሠረት ብር 196,546.98/አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር አምስት መቶ አርባ ስድስት ከዘጠና ስምንት ሣንቲም/ ካሣ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡